ሚያዝያ 26, 2021 የተከለሰ

# ኮቪድ-19: ለቶሮንቶ ነዋሪዎች መመሪያ

ይህ መመሪያ በኦንቶሪዮ አውራጃ በኮቪድ ምክንያት አውራጃውን ከእንቅስቃሴ ለመዝጋት ስለሚወሰደው መመሪያ እና ከሚያዝያ 8 ጀምሮ በቶሮንቶ ተግባራዊ ስለሚሆነው በቤት ውስጥ የመቆየት ትዕዛዝ ለነዋሪዎች መረጃ ይሰጣል።

ይህ መመሪያ ህጋዊ ምክር አይደለም፤ ነገር ግን እነዚህን መመሪያዎች መጣስ በአውራጃው መመሪያዎች መሰረት ቅጣት የሚያስከትል ጉዳይ ተደርጎ ይወሰዳል። ተግባራዊ ከሆኑት የአውራጃው ህጎች ጋር ተጣጥሞ ስለመከናውኑ ለማጣራት፣ ግለሰቦች እና ቢዝነሶች ተዛመጅ ህጎችን ማለትም Shutdown Zone provisions, Stay-at-Home order እና/ወይንም ህጋዊ ምክር ዋቢ ማድረግ አለባቸው። የአውራጃው የኮቪድ የእንቅስቃሴ ገደብ መመሪያ COVID-19 shutdown: enhanced public health and workplace safety measures በአውራጃው ድረ ገፅ ይገኛል።

ተግባር ላይ እንዲውሉ የወጡት የከተማው mask by-law እና physical distancing by-laws በፓርኮች እና ሰው በተሰበሰበበት ቦታ ተግባራዊነታቸው መቀጠል አለበት። የቫይረሱን ስርጭት reduce virus spread ለመቀነስ በህረተሰብ ጤና ጉዳይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን መከተል ጠቃሚ ነው። ስለ ኮቪድ-19 ጥያቄ ካልዎ የቶሮንቶ የህብረተሰብ ጤና ነፃ የስልክ መስመር 416-338-7600 መደወል ይችላሉ።

በቶሮንቶ ኮቪድ-19 እንዲቀንስ የበኩልዎን ስላደረጉ እናመሰግናለን።

| | **የእንቅስቃሴ ገደብ የሚደረግበት ዞን እና በቤት የመቆየት ትዕዛዝ** |
|---|---|
| **በቤት ውስጥ መሰብሰብ** | በቤት ውስጥ መቆየት ትዕዛዝ ከተጠሰው ምክንያት ውጪ በማንኛውም ጊዜ አሁን በሚኖሩበት ቦታ መቆየት አለብዎ። በቤትዎ ያለ ውጫዊ ቦታን ለምሳሌ አካላዊ ርቀትን መተግበር ወይንም ማስክ ማድረግ የሚያስችል ክፍት ክፍት ለምሳሌ የቤትዎን ጓሮ መጠቀም ይችላሉ።<br><br>በቤት ውስጥ የሚዘጋጁ ህዝባዊ ኩነቶች እና ማህበራዊ ስብሰባዎች- በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ካሉ ሰዎች እና ለብቻው ከሚኖር አንድ ሰው ውጪ አይፈቀድም።<br><br>ለብቻዎ የሚኖሩ ከሆነ፣ በመኖርያ ቤት ደረጃ ከአንድ መኖርያ ቤት ጋር ብቻ ግንኙነት ሊኖርዎ ይገባል። |
| **ከቤት ውጪ መሰብሰብ** | ከቤት ውጭ የሚዘጋጁ ህዝባዊ ዝግጅቶች እና ማህበራዊ ስብሰባዎች በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ የአንድ ቤተሰብ አባላት እና ብቻውን የሚኖር ሰው ካልሆነ በስተቀር አይፈቀዱም። |
| **ቤት ትምህርት** | በጣም ውሱን ለሆኑ የሚፈቀድ ቢሆንም፣ በትምህርት ሕጉ መሰረት መስፈርቱን የሚያሟሉ ትምህርት ቤቶች ተዘግተው ይቆሉ። |
| **ወደ ሌላ ክልሎች መሄድ** | በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ከክልል ወይንም ካሉበት አካበቢ ወጪ ጉዞ ማድረግ የለብዎትም። |
| **ሀይማኖታዊ አገልግሎቶች፣ ሰርጎች** | ለሰርግ፣ ቀብር ወይም ሀይማኖታዊ አገልግሎቶች ወይም ስርዓቶች ወይም ክብረ በአላት የሚከናወኑ የቤት ውስጥ ወይም ውጭ መሰባሰቦች ወደ 10 ሰዎች ወይም ከዛ ላነሱ ሰዎች |

ሚያዝያ 26, 2021 የተከለሰ

| | የእንቅስቃሴ ገደብ የሚደረግበት ዞን እና በቤት የመቆየት ትዕዛዝ |
|---|---|
| **እና የቀብር ስነ ስርአቶች** | የተወሰኑ ናቸው። <br><br> ሰርግን፣ ቀብርን ወይንም ሀይማኖታዊ ስርዓት ወይም ክብረ በአልን ተከትሎ በቤት ውስጥ ወይም ከቤት ውጭ የሚከናወን ማህበራዊ ስብሰባ አይፈቀድም። |
| **ችርቻሮ** | ሸቀጣ ሸቀጥ በችርቻሮ በሚሸጡ ሱቆች በአካል ገብቶ መግዛት አይቻልም። ቀድመው ያዘዙትን ዕቃ ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 3 ሰዓት ባለው ጊዜ ከሱቁ አንስቶ መሄድ ይፈቀዳል። ሁሉም ሸያጭ ደንበኛው ወደ ሱቅ ውስጥ ገብቶ ግዢ እንዳይፈፅም በሚያደርግ ሁኔታ መከናወን አለበት።  እቃ ለደንበኞች የሚደርስበት ሰዓት ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ 9 ሰዓት ባለው ጊዜ መሆን አለበት። <br><br> ሱቁ ሰው የመቻል አቅሙ 25 በመቶ ከቀነሰ በሱቅ ውስጥ በአካል ገብቶ ግብይት በሚከተሉት ቦታዎች መፈፀም ይቻላል፡ <br><br> • ፋርማሲ <br> • ሸቀጣሸቀጥ መሸጫዎች (ሱፐር ማርኬት፣ አመቺ ቦታ ያሉ ገበያዎች፣ በቤት ውስጥ ያሉ የአርሶ አደር ገበያዎች) <br> • የተወሰነ ሸቀጣሸቀጥ ለምሳሌ የተለያዩ ግሮሰሪዎች፣ የቤት እንስሳ ግብዓቶች፣ የቤት ማፅጃ፣ የጤና ግብዓቶች፣ የትምህርት ቤት ግብአቶች እና የቤት ደሕንነት መጠበቂያዎች የቅናሽ  እና በትልቅ ሳጥን እቃ መሸጫ ሱቆች <br> • መጠጥ የሚሸጡ ሱቆች (ቢራ፣ ወይን እንዲሁም ለስላሳ መጠጦች) <br> • ውጪ ያለ መናፈሻ እና ችግኝ ማፍያ <br> • በቤት ውስጥ ያለ ግሪን ሀውስ <br><br> በውጪ የሚከወኑ ግብይቶች የሚፈቀዱት፡ <br><br> • ምግብ በዋናነት የሚሸጡ ከሆነ <br> • ምርቶች ለደንበኛው የሚደርሱበት መንገድ ደንበኛው ውጪ እንዲቆይ ወይንም መኪና ማቆሚያ ዳር ቆሞ እቃውን መቀበል በሚያስችል መልኩ ከሆነ፣ እና <br> • አቅሙ ከ 25 በመቶ አይበልጥም <br><br> ሰው የመያዝ አቅሙ በ25 በመቶ ተገድቦ የሱቅ ውስጥ ግብይት በሚከተሉት ቦታዎች በቀጠሮ ማግኘት ይቻላል: <br><br> • የደህንነት እቃ አቅራቢ ሰቆች <br> • ኪራይ፣ ጥገና፣ የእንቅስቃሴ ወይንም የህክምማ ድጋፍ ወይንም አቅርቦት የሚሰጡ ቢዝነሶች <br> • የመነፅር እና ተዛማጅ እቃ መሸጫ ሱቆች |

ሚያዝያ 26, 2021 የተከለሰ

| | **የእንቅስቃሴ ገደብ የሚደረግበት ዞን እና በቤት የመቆየት ትዕዛዝ** |
| --- | --- |
| | • የቴሌኮሚውኒኬሽን አቅራቢዎች እና ችርቻሮ እቃ ሻጮች<br><br>በአውራጃው ህግ መሰረት ክፍት እንዲሆን ወደተፈቀደው ቦታ ማለትም ፋርማሲዎች ወይንም መያዝ የሚችለው የሰው አቅም ገደብ ወደተደረገባቸው ምግብ መሸጫ ሱቆች እንዲሁም በቀጥሮ እቃ ወደሚወስዱበት ቦታ ግለሰቦች መግባት ይችላሉ፡፡<br><br>እንዲከፈቱ የተፈቀደላቸው ሰዎች ደንበኞች ለራሳቸው የጤና ፍተሻ እንዲያደርጉ ማስታወቂያ መለጠፍ አለባቸው፡፡ ፍተሻውን ካላለፉ፣ ወደውስጥ መግባት የለብዎትም፡፡<br><br>የህክምና ሁኔታ ካለባቸው ሰዎች ወይንም በጣም ታዳጊ ሰዎች በስተቀር፣ በሱቅ ውስጥ ያሉት ሁሉም ሰዎች ማስክ ወይንም የፊት መሸፈኛ ጭንብል ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |
| **ሬስቶራንት** | በትዕዛት ይዞ መሄድ፣አልኮልን ጨምሮ እቃ መቀበል የሚፈቀድ ከሆነ፡፡<br><br>ከቤት ውጪ እና ውስጥ ምግብ መብላት አይፈቀድም፡፡ |
| **የግል ክብካቤ አገልግሎት** | የግል ክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎች ለምሳሌ የውበት ሳሎኖች፣ የወንዶች ፀጉር ቤት፣ የጥፍር ውበት በመጠበቂያ፣ ፀሀይ መሞቂያ፣ ንቅሳት ቤቶች እንዲሁም ሌሎች የውበት አገልግሎቶች እንዲንቀሳቀሱ አይፈቀድም፡፡ ባለሞያው የሚቆጣጠረው የህክምና ቀጠሮዎች ለምሳሌ ፊዚዮቴራፒ እና ማሳጅ ይፈቀዳሉ፡፡ |
| **መዝናኛ** | አንዳንድ የውጩ መዝናኛ ቦታዎች ፣ የተወሰነ ገደብ ተደርጎባቸው ለአገልግሎ ክፍት ናቸው፡፡ ክፍት ሆነው የሚቆዩ አገልግሎት መስጫዎች ሲጠቀሙ ወይም አካላዊ መራራቅ አስቸጋሪ በሚሆንበት አጋጣሚ የፊትና አፍንጫ መሸፈኛ ወይም የፊት መሸፈኛ ከቤት ውጭ መጠቀም በፅኑ ይመከራል፡፡ የማጠብያ አገልግሎት ቦታዎች ሲጠቀሙ እና ሰልፍ ሲሰለፉ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ መጠቀም ግድ ይላል፡፡<br><br>ክፍት የሆኑ አገልግሎት መስጫዎች፡<br><br>• ፓርኮችና ባህር ዳርቻዎች<br>• የህፃናት መጫወቻ ቦታዎች<br>• የእጥበት አገልግሎት መስጫዎች<br>• የውሻ መናፈሻ<br>• ፓርኮችና መዝናኛ ቦታዎች ላይ የሚገኙ መቀመጫዎች<br>• የማህበረሰብና አካባቢ የአትክልት ስፍራዎች<br><br>ከላይ ያልተጠቀሱ የውጭ መዝናኛ አገልግሎት መስጫዎች በአውራጃው ሕግ መሰረት ዝግ ሲሆኑ የሚከተሉትን ያካትታሉ፡ |

ሚያዝያ 26, 2021 የተከለሰ

| | የእንቅስቃሴ ገደብ የሚደረግበት ዞን እና በቤት የመቆየት ትዕዛዝ |
|---|---|
| | • የፒክኒክ ጠረጴዛዎች እና መጠለያዎች<br>• የጎልፍ መጫወቻ ቦታዎች<br>• የዲስክ ጎልፍ መጫወቻ ቦታዎች<br>• የስፖርት መጫወቻ ቦታዎችና ሜዳዎች (እነሱም የባስኬት እና ቴንስ ሜዳዎች፣ የእግር ኳስ ሜዳዎች፣ የቤዝቦል ሜዳዎች፣ የቦውሊን መጫወቻ ቦታዎች)<br>• የቢኤምኤክስ እና ስኬት ፓርኮች<br>• የቤት ውጭ አካል እንቅስቃሴ መስርያ ቁሳ ቁሶች<br>• ድራይ ፓድስ (ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ስፖርት መጫወቻ ቦታዎች)<br><br>ውጪ የሚሰሩ የአካል ብቃት ክፍለ ጊዜዎች እና ስልጠናዎች አይፈቀዱም።<br><br>የቤት ውስጥ ስፖርት እና የመዝናኛ አካላዊ እንቅስቃሴ ቦታዎች የተወሰነ ገደብ ተደርጎላቸው ዝግ ይሆናሉ (ለምሳሌ ባለሞያ እና ጥሩ እንቅስቃሴ ያላቸው አትሌቶች ፣ በኦንታሪኒ አካል ጉዳተኞች ተደራሽነት ህግ መሰረት አካላዊ ቴራፒ የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች) |
| **ቤተ መጻሕፍት** | ቤተመፃህፍት ክፍት ሲሆኑ ጥቅም ላይ የሚውሉትት ንክኪ ሳይኖር የሚነሱ እቃዎች ናቸው። መፃህፍት እና ሌሎች ከሰው ሰው የሚዘዋወሩ ቁሳቁሶች በስልክ ወይንም በኢንተርኔት ቅድመ ፕሮግራም አስይዞ መውሰድ ይችላል። |
| **የቤት እንስሳት ክብካቤ** | የቤት እንስሳ አገልግሎት መስጠት ይፈቀዳል።<br><br>የቤት እንስሳትን የማዋል አገልግሎት ለምሳሌ የቤት እንስሳትን የማንሸራሸር፣ የማፅዳት እና የማሰልጠን አገልግሎት። |
| **የመኖርያ ቤት አገልግሎ** | ህፃናትን፣ አረጋውያንን እና ተጋላጭ ሰዎችን ለመደገፍ የቤት ውስጥ የፅዳት እና የጥገና አገልግሎት ይፈቀዳል። |